### ሃያ ስምንተኛ ሐዲሥ

(ثلاثةٌ حقٌّ على اللهِ عونهم : المجاهدُ في سبيلِ اللهِ ، والْمُكَاتَبُ الذي يريدُ الأداءَ ، والناكحُ الذي يُرِيدُ العفافَ) (رواه الترمذي)

ከአቢ ሁረይራ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡- **" ሦስት ሰዎች አላህ ሊረዳቸው ግድ ነው፤ በአላህ መንገድ ታጋይ የሆነን ሰው፣ ከፍሎ ነፃ ለመውጣት ብሎ የተዋዋለን ባርያ እና ጥቡቅነትን በመሻት ያገባ ሰው፡፡"** ( ቲርሚዚ ዘግበዉታል፡፡)

### ከሐዲሡ ከምናገኛቸው ጠቃሚ ትምህርቶች

በአላህ መንገድ መታገል ያለው ትሩፋት፣ ለባርያው የአላህን እርዳታ እንደሚያስገኝ፣ አላህ عَزَّوَجَلَّ ዘንድ የላቀና የተከበረ ሥራዎች መካከል እንደሆነ፣

ከሐራም ራሱን ለመጠበቅ ብሎ የሚያገባ ሰው ያለው ትሩፋት፤ አላህ በጋብቻ ጣጣውና ወጪው ላይ ያግዘዋል፣ ይህም በቁርኣን ዉስጥ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

(وَأَنكِحُواْ ٱلۡأَيَٰمَىٰ مِنكُمۡ وَٱلصَّٰلِحِينَ مِنۡ عِبَادِكُمۡ وَإِمَآئِكُمۡۚ إِن يَكُونُواْ فُقَرَآءَ يُغۡنِهِمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ) (سورة النور 32)

{ከናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ። ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የሆኑትን (አጋቡ)። ድሆች ቢሆኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል።} (አን-ኑር ፡ 32)

ኢብኑ ዐባስ رَضِيَٱللَّهُعَنْهُ እንዲህ ብለዋል ፡- “አላህ በጋብቻ አበረታታቸው፤ በዚህ ቃሉም አዘዛቸው፡፡”

(وَأَنكِحُواْ ٱلۡأَيَٰمَىٰ مِنكُمۡ وَٱلصَّٰلِحِينَ مِنۡ عِبَادِكُمۡ وَإِمَآئِكُمۡۚ)

{ከናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ። ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የሆኑትን (አጋቡ)።} (አን-ኑር ፡ 32) ሀብታም እንደሚያረጋቸዉም ቃላ ገባላቸው፡፡

(إِن يَكُونُواْ فُقَرَآءَ يُغۡنِهِمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ) (سورة النور 32)

{ድሆች ቢሆኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል።} (አን-ኑር ፡ 32)
አቡበክር አስ-ሲዲቅ رَضِيَٱللَّهُعَنْهُ “ ከጋብቻ አንፃር አላህ ያዘዛችሁን ነገር ፈጽሙ፤ እሱ የገባላችሁን የሀብታምነት ቃል ይሞላላችኋልና፡፡ እሱ እንዲህ ብሏል ብለዋል፡፡

(إِن يَكُونُواْ فُقَرَآءَ يُغۡنِهِمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ) (سورة النور 32)

{ድሆች ቢሆኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል።} (አን-ኑር ፡ 32)
ከኢብኑ መስኡድ رَضِيَٱللَّهُعَنْهُ እንደተወራው “ሲሳይን በጋብቻ ዉስጥ ፈልጉ፡ ፡ አላህ እንዲህ ይላልና ብለዋል

(إِن يَكُونُواْ فُقَرَآءَ يُغۡنِهِمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ) (سورة النور 32)

{ድሆች ቢሆኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል።} (አን-ኑር ፡ 32) (ኢብኑ ጀሪር እንደዘገቡት)
አንቀፁ ላዩን ሲታይ የሚያመለክተው እያንዳንዱ ያገባ ድሃ በሀብት ቃል እንደተገባለት ነው፡፡ የአላህ ቃል ደግሞ ሊፈፀም ግድ ነው፡፡ አንድ ድሃ

አግብቶ ሀብታም ያልሆነ እንደሆነ የአላህ ቃል ዉሸት ነው ማለት አይደለም፤ አላህ ከዚህ የጠራ ነው፡፡ ምክንቱም የሰውዬው ሀሳብ ችግር ስለነበረበት ሊሆን ይችላል፡፡ አላህ በመልካም እሳቤ ላገቡት ነው ቃል የገባው፡፡ ስለዚህ አግብቶ ሀብታም ያልሆነ ሰው ተመልሶ ራሱን ይመርምር፣ ይውቀስም፡፡

## መልመጃ

1- ነቢዩ ﷺ ሦስት ሰዎችን አላህ ሊረዳቸው ግድ ነው ብለዋል፤ በሦስቱ ሰዎች መካከል የሚያስተሳስር ነገር ምንድነው?

--------------------------------------------------

2- አላህ ጋብቻን የሚፈልግን ሰው ሀብታም ሊያደርገው ቃል ገብቷል፤ ግና ብዙ ያገቡ ሰዎች ድሆች ሆነው እናያለን፡፡ ይህን ብዥታ እንዴት መግፈፍ ይቻላል?

----------------------------------------------

3- ከላይ ከተጠቀሱት ዉጭ አላህ በራሱ ላይ ግድ ያደረጋቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ጥቀስ፣

-----------------------------------------------------

### ሃያ ዘጠነኛ ሐዲሥ

(إِنَّ الدُّنْيَا حُلْوَةٌ خَضِرَةٌ، وإِنَّ اللَّهَ مُسْتَخْلِفُكُمْ فِيهَا، فَيَنْظُرُ كيف تَعْمَلُونَ، فَاتَّقُوا الدُّنْيَا وَاتَّقُوا النِّسَاءَ، فإِنَّ أَوَّلَ فِتْنَةِ بَنِي إِسْرَائِيلَ كَانَتْ فِي النِّسَاءِ)

(رواه مسلم)

ከአቢ ሰዒድ አል-ኹድሪይ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው ነቢዩ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡- “ይህች ዓለም ጣፋጭ አረንጓዴ ናት፡፡ አላህም በሷ ዉስጥ ምትኮች አድርጓችኋል፡፡ ምን እንደምትሠሩም ያያል፡፡ ይህችን ዓለም ተጠንቀቁ፣ ሴቶችንም ተጠንቀቁ፡፡ የበኒ ኢስራኢሎች የመጀመርያው ፈተና በሴት ነበር፡፡” (ሙስሊም ዘግበዉታል፡፡)[13]

### ከሐዲሡ ከምናገኛቸው ጠቃሚ ትምህርቶች

1- ይህች ዓለም ከመጨረሻው ዓለም ስትነፃፀር ምንም ማለት አይደለችም፣ እሷ መሸጋገርያ ናት፣ ለመጨረሻው ዓለምም መዝሪያ ቦታ ናት፡፡

2- በዚህች ዓለም ከመታለል እና ወደ ሴቶች ከማዘንበል ማስጠንቀቅ ተላልፎበታል፡፡ ለተፈተነ ሰው ሁሉ ትልቁ ፈተናዎች እነርሱ ናቸው፡፡

---

13 -ሰዕድ ኢብኑ ማሊክ ኢብኑ ሲናን አል-አንሷሪይ ይባላል፡፡ በዕድሜ ትናንሽ ከሆኑ እንዲሁም ከምርጥ ሶሐቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ብዙ ሐዲሦችን በማውራት ይታወቃል፡፡ ሊቅ ነው፣ ተመራማሪ እና ሙፍቲም ነው፡፡ ከነቢዩ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ጋር በኸንደቅ ዘመቻ እና ከዚያም በኋላ በነበሩት ላይ ተሳትፏል፡፡

በሌላ ሐዲሥም የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ከዱንያ አስጠንቅቀዋል፡

- “ከኔ በኋላ የምፈራላችሁ ነገር ፤ ከዚህች ዓለም ዉበትና ብልጭልጭ ነገር እና ጌጥ የሚሰፋላችሁን ነገር ነው፡፡” ብለዋል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል፡፡)

ከሴቶች ማስጠንቀቅም በብዙ ሐዲሣቸው ዉስጥ ተላልፏል፡፡ እንዲህ ብለዋል፡ “ከኔ በኋላ በወንዶች ላይ ትልቅ ጉዳት የሚያመጣ ፈተና ከሴቶች በላይ አልተውኩም፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል፡፡)

3- ነቢዩ ﷺ ለሕዝባቸው መስተካከል ትልቅ ጉጉት አላቸው፤ ለጥፋት ከሚዳርጓቸው ነገሮች ሁሉ አስጠንቅቀዋቸዋል።

4- እጅግ ከባዱና ብርቱው ፈተና የሴቶች ፈተና ነው፡፡ ፈተናቸው ከባድ ነው፡፡ በዚህ ፈተና ላይ መውደቅም አደጋው ከባድ ነው፡፡ እነርሱ የሸይጧን ሴራ ማጥመጃዎች ናቸው፡፡ በነርሱ አማካይነት ሸይጧን ስንቱን ጠልፎ የስሜቱ ምርኮኛ አድርጓል! ፣ በወንጀሉ አስሮታል፣ ስንቱስ ከዚህ ሁኔታ መላቀቅ ከብዶታል!፡፡ ከነርሱ ቢጠነቀቅ፣ የሚታማበትን መግቢያ ባይገባ፣ ለዚህ መከራ ባይዳረግ፣ በአላህ ቢታገዝ፣ ከዚህ ፈተና በዳነ ነበር፡፡ ከዚህ ችግርም በተላቀቀ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ነቢዩ ﷺ በዚህ ሐዲሥ ዉስጥ በተለየ ሁኔታ ያስጠነቀቁት፡፡

## መልመጃ

1- የኢስላም ሸሪዓ ከዱንያ ፈተና በማስጠንቀቅ ረገድ ምን ያህል ትኩረት እንደሠጠ ግለጽ፣

..........................................................................................

2- ስለ ሙስሊሟ ሴት ባይተዋር ማድረግ ዙሪያ አጠር ያለ ጥናት ፃፍ፣ ጉዳዩን በምን መልኩ መከላከልና ማከም ይቻላል፣

..........................................................................................

3- ይህንን ሐዲሥ እና ሌላዉንም መሠረት በማድረግ ነቢዩ ﷺ ለሕዝባቸው ያላቸዉን የመስተካከል ጉጉት ግለጽ፣

..........................................................................................

## ሰላሳኛ ሐዲሥ

(أخَذَ رَسولُ اللَّهِ صلَّى اللهُ عليه وسلَّم بمَنْكِبِي، فَقَالَ: كُنْ في الدُّنْيَا كَأنَّكَ غَرِيبٌ أوْ عَابِرُ سَبِيلٍ. وكانَ ابنُ عُمَرَ يقولُ: إذَا أمْسَيْتَ فلا تَنْتَظِرِ الصَّبَاحَ، وإذَا أصْبَحْتَ فلا تَنْتَظِرِ المَسَاءَ، وخُذْ مِن صِحَّتِكَ لِمَرَضِكَ، ومِنْ حَيَاتِكَ لِمَوْتِكَ)

ከዐብደላህ ኢብኑ ዑመር رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ትከሻዬን ያዙኝና እንዲህ አሉኝ:-

“በዚህች ምድር ላይ እንደ ባይተዋር እንግዳ ወይም እንደ መንገድ አቋራጭ ሁን፡፡ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ይሉ ነበር :- “ካመሸህ ንጋትን አትጠብቅ፤ ካነጋህ ደግሞ ምሽትን አትጠብቅ፡፡ ከጤንነትህ ለሕመምህ፣ ከሕይወትህ ደግሞ ለሞትህ ያዝ፡፡” (ቡኻሪ ዘግበውታል)[14]

---

14 -ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር ኢብኑ አል-ኸጧብ ይባላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ባልደረባ ነው፡፡ አል-ኸንደቅ ዘመቻ ላይ እንዲሁም ከዚያ በኋላም ተሳትፎ ነበረ፡፡ ዕድሜው ትንሽ ስለነበር በድርም ሆነ ኡሑድ ዘመቻ ላይ አልተሳተፈም፡፡ ስልሳ ዓመት ሙሉ በሙፍቲነት አገልግሏል፡፡ በመጨረሻ የሕይወት ዘመኑ አካባቢ ዐይኑ ታዉሮ ነበር፡፡ በመካ ከሶሐቦች ሁሉ መጨረሻ ላይ የሞተው እሱ ነው፤ በ73 ዓመተ ሂጅራ፡፡

## ከሐዲሡ ከምናገኛቸው ጠቃሚ ትምህርቶች

1- ከዱንያ ላይ መታቀብ፣ የሰው ልጅ እሷን የዘላለማዊ መኖርያ አገር አድርጎ ሊያስባት አይገባም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "በዚህች ምድር ላይ እንደ ባይተዋር እንግዳ ወይም እንደ መንገድ አቋራጭ ሁን፡፡" ብለዋልና፡፡

2- የአላህ መልዕክተኛ ﷺ አሳማኝ የሆኑ ምሳሌዎችን በማቅረብ ባማረ መልኩ የሚያስተምሩበት ሁኔታን እንማራለን፡፡ ለምሳሌ "ከዱንያ ታቀብ፣ ወደርሷ አታዘንብል" እና የመሣሠሉትን ቢሉ "በዚህች ምድር ላይ እንደ ባይተዋር እንግዳ ወይም እንደ መንገድ አቋራጭ ሁን፡፡" የሚለዉን ያህል መልዕክት አያስተላልፍም፡፡

3- ካነጋህ አመሻለሁ፣ ካመሸህ ደግሞ አነጋለሁ ብለህ ተስፋ አታድርግ፡፡ ስንት ሰው አለ ያነጋ ያላመሸ፤ ስንት ሰው አለ ያመሸ ያላነጋ! ፡፡ ስንት ሰው አለ ልብሱን ጀናዛ አጣቢ ያወለቀለት! ፡፡ ስንት ሰው አለ ቤተሰቦቹ ምሳ ወይም እራት አዘጋጅተዉለት ሳይበላ የሞተ! ስንት ሰው አለ ከፍራሹ ሳይነሳ በዚያው የቀረ!!

የሰው ልጅ ምኞትና ተስፋን ማስረዘም የለበትም፡፡ ሁሌም በተጠንቀቅ እና በቁርጠኝነት ሁኔታ ላይ ነው መሆን ያለበት፡፡

4- የሰው ልጅ ከጤንነቱ ለሕመሙ መያዝ አለበት፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ በጤናው ጊዜ የአምልኮ ተግባራት ይገሩለታል፡፡ ከተከለከለው ነገር ይርቃል፡፡ ግን የታመመ እንደሆነ በተቃራኒው ነው የሚሆነው፡፡ እንዲሁ የሰው ልጅ ከሕይወቱ ደግሞ ለሞቱ መያዝ አለበት፡፡ ጤናማ የሆነ፣ ልቦናው የሰፋ፣ ነፍሱ ፈታ ያለች፣ ሀሳቡ ከፍ ያለ፣ ጊዜ እና ጤና ያለው

በርግጥ መጠቀም አለበት፡፡ ግና ይህን ሁሉ የሚያባክኑ ሰዎች አቤት መብዛታቸው!!

### መልመጃ

1- ኢብኑ ዑመር ይህን ሐዲሥ ተግባር ላይ ከማዋል አንጻር በምን መልኩ ነው የተመከረው?

............................................................................................

............................................................................................

2- ይህ ሐዲሥ እና ተመሳሳዮቹ በሸሪዓው ዉስጥ ሊያስቀምጡት የሚችሉት መርህ ምንድነው?

............................................................................................

............................................................................................

3- የሰው ልጅ ከወጣትነቱ ለሽምግልና ዕድሜው፣ ከሀብታምነቱ ለድህነት ጊዜው፣ ከጤናው ለሚታመምበት ሁኔታው ሊወስድ የሚችለው እንዴት ነው?

............................................................................................

............................................................................................

### ሰላሳ አንደኛ ሐዲሥ

ከአነስ ኢብኑ ማሊክ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

(حُفَّتِ الجَنَّةُ بالمَكارِهِ، وحُفَّتِ النَّارُ بالشَّهَواتِ)

**"ጀነት የተከበበችው በሚያስጠሉ ነገሮች ነው፤ እሣት የተከበበችው ስሜት በሚስቡ ነገሮች ነው፡፡"** (ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበዉታል፡፡)

### ከሐዲሡ ከምናገኛቸው ጠቃሚ ትምህርቶች

1- ጀነት የሚገኘው ለነፍስ በሚከብዱ ነገሮች ላይ በመታገስ ነው፣ ከእሣት መዳን የሚቻለው ነፍስን ክልክል ከሆነው ስሜት በመለጎም ነው፡፡

2- የጀነት መንገድ አስፈሪ ነው፣ ተጓዥ የለበትም፡፡ ነቢዩ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ "ጀነት በሚያስጠሉ ነገሮች ተከበበች" ማለታቸው ብቻ በቂ ነው፡፡ ይህ ለነፍስ የሚከብድ አስቸጋሪ የሆነ ነገር የሚቀለው ከጀርባው ጀነት እንዳለ ሲታሰብ ነው፡፡

3- ሐዲሡ የነገሮች መጨረሻን ስለመጠበቅ ያበረታታል፡፡ ድካም መጨረሻው ዕረፍት ሲሆን ቀልሎ ይታያል፡፡ አዋቂ ማለት የአሁኑን አላፊዉን ሁኔታ ሳይሆን የነገሮችን መጨረሻ የተመለከተ ነው፡፡ ጠቢባን እንዳሉትም "ዕረፍት በዕረፍት አይገኝም፡፡"

4- ወደ እውነት የሚጣራ ተጣሪ ለችግር የተጋለጠ ነው፡፡ መንገዱ በአበባ የተነጠፈ አይደለም፡፡ ባይሆን ጉዳዩ ነቢዩ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዳሉት ነው፡-

**"ጀነት የተከበበችው በሚያስጠሉ ነገሮች ነው፤ እሣት የተከበበችው ስሜት በሚስቡ ነገሮች ነው፡፡"**

5- ጀነትም ይሁን እሣት የተፈጠሩ ናቸው፡፡ አሁንም ድረስ አሉ፡፡ አያልቁም፣ ለዘላለምም አይጠፉም፡፡ የአህሉ ሱንና ወል-ጀማዓ የአመለካከት መንገድ እንዲህ ነው፡፡ ሙዕተዚላንና የቀደርያን አመለካከት ይቃረናል፡፡

6- በዚህ ላይ ከቁርኣንም ሆነ ከሐዲሥ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ أُعِدَّتۡ لِلۡمُتَّقِينَ﴾

﴿ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ሆነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትሆን ተቻኮሉ።﴾ (ኣሊ ዒምራን ፡ 133)

﴿ያችን ﴿فَٱتَّقُواْ ٱلنَّارَ ٱلَّتِي وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُۖ أُعِدَّتۡ لِلۡكَٰفِرِينَ﴾ መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች የሆነችውን እሳት ተጠበቁ፤ ለከሀዲዎችም ተደግሳለች።﴾(አል-በቀረህ ፡ 24)

ቡኻሪ እና ሙስሊም ስለ ኢስራእ ታሪክ በተወራው ሐዲሥ አነስን رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُ በመጥቀስ እንዳስተላለፉት በሐዲሡ መጨረሻ ላይ እንዲህ የሚል ይገኛል፡-

(ثُمَّ انْطَلَقَ بِي جِبْرِيلُ حتَّى نَأْتِيَ سِدْرَةَ الْمُنْتَهَى فَغَشِيَهَا أَلْوانٌ لا أَدْرِي ما هي؟ قالَ: ثُمَّ أُدْخِلْتُ الجَنَّةَ، فإذا فيها جَنابِذُ اللُّؤْلُؤَ، وإذا تُرابُها المِسْكُ)

“ከዚያም ጂብሪል ይዞኝ ሄደ፤ ሲድረተል ሙንተሃ እስኪደርስ ድረስ፡፡ በተለያዩ ቀለሞች የተሸፈነች ናት፡፡ ምን እንደሆነች አላወቅኩም፡፡ ከዚያም ጀነት ገባሁኝ፤ ጣርያዋ እንቁ ነው፣ አፈሯ ደግሞ ሚስክ ነው፡፡”

በቡኻሪ እና ሙስሊም ዘገባ ከዐብደላህ ኢብኑ ዑመር رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

(إِنَّ أَحَدَكُمْ إذا ماتَ عُرِضَ عليه مَقْعَدُهُ بالغَداةِ والْعَشِيِّ، إنْ كانَ مِن أَهْلِ الجَنَّةِ فَمِنْ أَهْلِ الجَنَّةِ، وإنْ كانَ مِن أَهْلِ النَّارِ فَمِنْ أَهْلِ النَّارِ، يُقالُ :هذا مَقْعَدُكَ، حتَّى يَبْعَثَكَ اللَّهُ إلَيْهِ يَومَ القِيامَةِ)

**"አንዳችሁ የሞታችሁ እንደሆነ መቀመጫው ጠዋትና ማታ ይቀረብለታል፤ የጀነት ሰዎች ከሆነ የጀነት ነው፤ ከእሳት ሰዎች ከሆነ የእሣት ነው፡፡ ይህ መቀመጫህ ነው፤ አላህ የቂያማ ቀን እስኪቀሰቅስህ ድረስ፡፡"** ይባላል፡፡

በቡኻሪ እና ሙስሊም ዘገባ ከዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُ እንደተወራው እንዲህ አለ፡- በአላህ መልዕክተኛ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ዘመን ፀሐይ ተጋረደች አለና ሐዲሡን አወሳ፡፡ በዚሁ ሐዲሥ ዉስጥ

(إِنِّي رَأَيْتُ الجَنَّةَ، فَتَنَاوَلْتُ عُنْقُودًا، ولو أَصَبْتُهُ لَأَكَلْتُمْ منه ما بَقِيَتِ الدُّنْيَا، وأُرِيتُ النَّارَ، فَلَمْ أَرَ مَنْظَرًا كَاليَومِ قَطُّ أَفْظَعَ)

**"እኔ ጀነትን አየሁ የወይን ዘለላ አነሳሁ፤ ብታገኙት ኖሮ ይህች ዓለም እስካለች ድረስ ትበሉት ነበር፡፡ እሣትንም አየሁ፤ የዚያ ዓይነት አስደንጋጭ እይታ ፈጽሞ አይቼ አላውቅም፡፡"** የሚል ይገኛል፡፡

**መልመጃ**

1- በሐዲሡ ዉስጥ የታየዉን የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) የቋንቋ ምጥቀት ሁኔታን ግለጽ፣

..............................................................................................

..............................................................................................

2- ስሜት በሙስሊም ወጣት ላይ ስለሚያሳድረው ጠባሳ አጭር ጥናት ፃፍ፣

..............................................................................................

..............................................................................................

3- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ጠቅላይ ንግግር የተሠጡ መሆናቸዉን የሚያመለክቱ የተወሰኑ ነቢያዊ ሐዲሦችን ጥቀስ፣

..............................................................................................

..............................................................................................